## ቅሬታን እንዴት ፋይል ማድረግ እችላለሁ?

መድልዎ በሚከለክል በታይትል VI ደንቦች ወይም ተመሳሳይ ህጎች መሰረት መድልዎ ደርሶብኛል የሚል እምነት ቢኖርብዎ፣ ተደረገ የተባለው የመድልዎ ፍጻሜ(ዎች) ከተደረገ(ጉ) በኋላ ባሉት 180 ቀናት ውስጥ፣ ወይም የመድልዎ እርምጃ(ዎች) መፈጸማቸው በተገነዘቡበት ጊዜ፣ ቅሬታዎን በጽሁፍ ፋይል ማድረግ ይችላሉ።

ቅሬታው የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡

1. ስምዎ፣ አድራሻዎ፣ እና የቴሌፎን ቁጥርዎ። ሌላ ሰው በመወከል ፋይል እያደረጉ ከሆነ እየወከሉት ያለውን ሰው ስም፣ አድራሻ፣ የቴሌፎን ቁጥርና እየወከሉት ካለ ሰው ጋር ያለዎት ግንኙነት (ለምሳሌ፣ ጓደኛ፣ ጠበቃ፣ ወላጅ፣ ወዘተ)፣
2. ተደረገ የተባለው የመድልዎ እርምጃ(ዎች) የተፈጸመበት ቀን፣
3. በእርስዎ ላይ መድልዎ ፈጽሟል ብለው የሚያምኑት ኤጀንሲ፣ ተቋም ወይም ቢሮ ስምና አድራሻ፣
4. የኤጀንሲው ተወካይ(ዮች) ስም(ሞች) እና መገኛ መረጃ፣ የሚታወቅ ከሆነ፣
5. ተደረገ የተባለው የመድልዎ እርምጃ(ዎች) እና ለምን መድልዎ ደርሶኛል ብለው እንደሚያምኑ መግለጫ (በተቻለዎት መጠን በርካታ መረጃን ያካትቱ)፣
6. ተደረገ(ጉ) ያሉዋቸውን ነገር(ሮች) ለመደገፍ ወይም ለማብራራት ይረዳ ዘንድ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ዲ.ዲ.ኦ.ቲ. ማግኘት የሚችለው የማንኛውም ሰው ስምና መገኛ መረጃ፣ እና
7. ፊርማዎ።

**እባክዎ ቅሬታዎችዎን በዚህ ብሮሹር ጀርባ ወዳለው የዲ.ዲ.ኦ.ቲ. አድራሻ ይላኩ።**

## ዲ.ዲ.ኦ.ቲ. ቅሬታዬን ከተቀበለ በኋላ ምን ያደርጋል?

ከደረሰ በኋላ ቅሬታዎ በዲ.ዲ.ኦ.ቲ. የፍትሀዊነት እና ማካተት ክፍል (ኢኩይቲ ኤንድ ኢንክሉዥን ዲቪዥን) ዘንድ ይመዘገባል። ከትራንዚት ጋር ተያያዥነት የሌላቸው ዲ.ዲ.ኦ.ቲ. ወይም የዲ.ዲ.ኦ.ቲ. ንኡስ-ተቀባይ እንደ ምላሽ ሰጪ በማድረግ የለዩ የታይትል VI ቅሬታዎች ወደ ፌደራል ሀይወይ አድሚኒስትሬሽን (ኤፍ.ኤች.ዳብሊው.ኤ.) ለሂደት ይተላለፋሉ። ከትራንዚት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ዲ.ዲ.ኦ.ቲ. ወይም የዲ.ዲ.ኦ.ቲ. ንኡስ-ተቀባይ የሚከሱ ቅሬታዎች ወደ ፌደራል ትራንዚት አድሚኒስትሬሽን (ኤፍ.ቲ.ኤ.) ለሂደት ይተላለፋሉ። ዲ.ዲ.ኦ.ቲ. የሁሉም የተቀባላቸውና ሂደት ያደረጋቸው ቅሬታዎች ቅጂዎች በመስሪያ ቤቱ ለሶስት አመታት ያህል ይከታተላል ይጠብቃልም። እነዚህ ደንቦች በቀጥታ ወደ ዩ.ኤስ. ዲፓርትመንት ኦፍ ትራንስፖርቴሽን ይፋዊ ቅሬታ ፋይል የማድረግ መብትዎ ወይም የግል ጠበቃ ከመፈለግ አይገድቡም።

## መብቶቼ በመጠቀሜ ምክኒያት ብቀላ የደረሰብኝ ቢሆንስ?

ዲ.ዲ.ኦ.ቲ.ና ከዲ.ዲ.ኦ.ቲ. ፈንድ የሚያገኙ ህገወጥ የሆነ ፖሊሲ ወይም ልምድ በመቃወምዎ፣ ክስ በመመስረትዎ፣ ምስክርነት በመስጠትዎ ወይም በታይትል VI መሰረት በቅሬታ እርምጃ በመሳተፍዎ ምክኒያት እርስዎን ወይም ማንኛውም ሰው ከመበቀል የተከለከሉ ናቸው።

በቀል ደርሶብኛል የሚል እምነት ቢኖርብዎ ወዲያውኑ የዲ.ዲ.ኦ.ቲ. የፍትሀዊነትና ማካተት ክፍል (ኢኩይቲ ኤንድ ኢንክሉዥን ዲቪዥን) ያግኙ።



*ለተጨማሪ መረጃ ወይም ቅሬታ ፋይል ለማድረግ እባክዎ የሚከተለውን ያግኙ፡*


**District Department of Transportation (ዲስትሪክት ዲፓርትመንት ኦፍ ትራንስፖርቴሽን)**
**Office of the Director**
**(ኦፊስ ኦፍ ዚ ዲረክተር)**
**Equity and Inclusion Division**
**(ኢኩይቲ ኤንድ ኢንችሉዥን ዲቪዥን)**
**250 M Street SE, 8th Floor**
**Washington, DC 20003**
**ቴሌፎን፡ (202) 673-6813**
**ddot@dc.gov**


***ሁሉም ዘሮች (ሬስስ) ሰርተው በከፈሉት ግብር የተበረከቱ የህዝብ ፈንዶችን፣ ዘር መሰረት ባደረገ መድልዎን በሚያበረታታ፣ ስር እንዲሰድ በሚያደርግ፣ በሚደጉም፣ ወይም ውጤት በሚያመጣ ማንኛውም መልክ ፈንዶቹ መባከን እንደሌለባቸው ቀላል ፍትህ (ሲምፐል ጀስቲስ) ያስገድዳል።***

- ፕረዚደንት ጃን ኤፍ. ከነዲ

District Department of Transportation

# በ1964ቱ የፍትሐብሔር መብቶች ህግ በታይትል VI ስር ያለብዎ መብቶች



**"ማንኛውም ሰው በአሜሪካ በዘሩ፣ የቆዳ ቀለሙ፣ ወይም በብሔራዊ መነሻው ምክኒያት ከመሳተፍ ሊገለል፣ ከጥቅማ ጥቅሞች ሊታገድ፣ ወይም በማንኛውም የፌደራል የፋይናንስ ድጋፍ በሚያገኝ ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ መድልዎ ሊደርስበት አይገባም።"**

**42 U.S.C. §2000d**

Government of the District of Columbia
MURIEL BOWSER, MAYOR

## ታይትል VI ምንድን ነው?

ታይትል VI የ1964ቱ የፍትሐብሔር መብቶች ህግ (ታይትል VI) ግለሰቦች በማንኛቸውም የፌደራል እርዳታ የሚያገኙ ፕሮግራሞች በዘራቸው፣ በቆዳ ቀለማቸው ወይም በብሔራዊ መሰረታቸው መሰረት ካደረገ መድልዎ የሚከላከል የፌደራል ህግ ነው።

## በታይትል VI መሰረት መድልዎ የሚባል ምንድን ነው?

በአመሪካ ሁሉም ሰው ጥቅማ ጥቅሞች በማግኘት ዘንድ በእኩል የመያዝና የፌደራል እርዳታ በሚያገኙ ኤጀንሲዎች በሚሰጡ ፕሮግራሞች፣ አገልግሎቶችና እድሎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አለው።

አንድ ሰው ወይም የተወሰነ ቡድን በዘር፣ በቆዳ ቀለም፣ በብሔር መሰረት፣ በጾታ፣ በእድሜ ወይም በአካል ጉዳተኝነት ምክኒያት የመንግስት ጥቅማ ጥቅም ወይም አገልግሎት ሲከለከል በታይትል VI እና ተመሳሳይ ህጎች መሰረት መድልዎ ተከሰተ ሊባል ይችላል።

በታይትል VI መሰረት መድልዎ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡

- ግለሰብን ወይም ቡድንን የሚገባውን ማንኛውም የፕሮግራም አገልግሎት፣ የፋይናንስ እርዳታ ወይም በፕሮግራሙ መሰረት የሚገኝ ጥቅማ ጥቅም መከልከል፣
- በሚቀርብ አገልግሎት ወይም ጥቅማ ጥቅም ጥራት፣ ብዛት ወይም አቀራረብ በተመለከተ አንድን ሰው በተለየ መልኩ ማስተናገድ፣ እና
- አንድን ሰው ወይም ቡድን እንደ የማህበረሰብ እቅድ ወይም አማካሪ ስብሰባ/እንቅስቃሴ፣ ወይም በተመሳሳይ አካል እንዳይሳተፍ መከልከል።

## ታይትል VI ማክበር ያለበት ማን ነው?

የዲ.ዲ.ኦ.ቲ ሰራተኞች (ስታፍ)፣ ኮንትራክተሮች፣ አማካሪዎች (ኮንሳልታንትስ)፣ አቅራቢዎች፣ እና ሌሎች የፌደራል ፈንድ ተቀባዮች ታይትል VI ያሰፈረውን ሟሟላት ይገባቸዋል። የፌደራል ፈንድ ውሎች ታይትል VI ሟሟላት ያስፈልጋል የሚል መደበኛ አንቀጽ ማካተት ይኖርባቸዋል። የዲ.ዲ.ኦ.ቲ ተቋራጮች ከፌደራል-ድጋፍ የሚያደርግበት የህይወይ ግንባታ ፕሮጀክቶች ወይም ሌላ የፌደራል እርዳታ የሚደረግባቸው ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ ንኡስ-ተቋራጮች ሲመርጡና ሲያቆዩ መድልዎ ከመፈጸም የተከለከሉ ናቸው።

## የዲ.ዲ.ኦ.ቲ. ታይትል VI ፖሊሲና ዋስትናዎች

ዲ.ዲ.ኦ.ቲ. ፕሮግራሞቹና እንቅስቃሴዎቹ ሲተገብር ማንኛውም ሰው በዘር፣ በቆዳ ቀለም፣ በብሔር መሰረት፣ በጾታ፣ በእድሜ ወይም በአካል ጉዳት መሰረት፣ በታይትል VI እና በተመሳሳይ ህጎች በሰፈረው መሰረት ከተሳትፎ እንደማያገል፣ ጥቅማ ጥቅሞች እንደማይከለክል፣ ወይም መድልዎ እንደማያደርስ ያረጋግጣል።





## የማህበረሰብ ተሳትፎ

ዲ.ዲ.ኦ.ቲ. አካታች የሆነ፣ የማህበረሰብ አባላት በሁሉም የፕሮጀክቱ ደረጃዎች- የህንጻ እቅድ ከማውጣት እስከ የፕሮጀክቱ መጨረሻ የሚዘልቅ- ንቁ ድምጽ እንዲኖራቸው የሚፈቅድ የማህበረሰብ ተሳትፎ ፕሮግራም ያበረታታል ይደግፋልም።

**የታይትል VI ደንቦች፣ ከቁልፍ የአከባቢና ትራንስፖርቴሽን ህጎች ጋር፣ በትራንስፖርቴሽን ውሳኔ-መውሰድ ሂደት ወቅት ጉዳት የደረሰባቸው ወገኖች ቅድመ-ተሳትፎ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣል። እንደነ አናሳ (ማይኖሪቲ)፣ አነስተኛ-ገቢ ያላቸው፣ አካል ጉዳተኛ የሆኑ፣ ውሱን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ያላቸው እና ሌሎች የተደራሽነት እንቅፋቶች የሚያጥሟቸው ባብዛኛው የሚያስፈልጋቸው አገልግሎት የማያገኙ ማህበረሰቦች ለመድረስና ለማሳተፍ ልዩ ትኩረት ይሰጣል።**



## ታይትል VI እና የአከባቢ ፍትህ

የስራ አስፈጻሚ ትዕዛዝ (ኤክዘኩቲቭ ኦርደር) 12898፣ ለአናሳና አነስተኛ-ገቢ ላላቸው ህዝቦች የአከባቢ ፍትህ ለመፍታት የወጡ የፌደራል እርምጃዎች፣ ኤጀንሲዎች በአናሳና ዝቅተኛ-ገቢ ያላቸው ማህበረሰቦች የሚጠቀሙባቸው ፕሮግራሞቻቸው፣ ፖሊሲዎቻቸው፣ እና እንቅስቃሴዎች ተመጣጣኝ ያልሆነ ከፍተኛ ወይም ጎጂ የሰው ጤናንና የአከባቢ ጉዳት የሚያመጡ በመለየትና ችግሮቹን በመፍታት የአከባቢ ፍትህ እንዲቀዳጁ በማስገደድ በታይትል VI ትኩረቱ አድርጓል።

**ዲ.ዲ.ኦ.ቲ. የአከባቢ ፍትህ መርሆች በፖሊሲዎቹ፣ እቅዱና ፕሮጀክት በማዳበር እንቅስቃሴዎች ያስገባል፣ ይህ የሚያደርገው በከተማዋ ባሉ አናሳና አነስተኛ-ገቢ ያላቸው ማህበረሰቦች ሚዛናዊ ያልሆነ ጫና እንደማያሳድር ለማረጋገጥ ነው።**

## ውሱን እንግሊዝኛ ችሎታ ያላቸው/እንግሊዝኛ ቋንቋ የማይችሉ (ኤል.ኢ.ፒ./ኤን.ኢ.ፒ.) የሚባሉ እነማን ናቸው?

ኤል.ኢ.ፒ. የሚባል እንግሊዝኛ እንደ መጀመሪያ ቋንቋ የማይናገር፣ ውሱን የሆነ የማንበብ፣ የመናገር፣ የመጻፍ ወይም የመረዳት ችሎታ ያለው ሰው ነው። ኤን.ኢ.ፒ. የሚባል በማንኛውም ደረጃ እንግሊዝኛ መናገርና መረዳት የማይችል ሰው ነው።

የስራ አስፈጻሚ ትእዛዝ (ኤክዘኩቲቭ ኦርደር) 13166 የፌደራል እርዳታ የሚያገኙ ድርጅቶች ኤል.ኢ.ፒ. የሆኑ ሰዎች እንግሊዝኛ የሚችሉ ሰዎች የሚያገኟቸው አገልግሎቶችን ትርጉም ያለው ተደራሽነት እንዲያገኙ እንዲያደርጉ ያስገድዳል።

በ2004 የወጣው የዲ.ሲ. ላንጉጅ አክሰስ (የቋንቋ ተደራሽነት) ህግና በመቀጠል የተላለፉ ማሻሻያዎች መሰረት አገልግሎት ከሚያገኘው፣ ለአገልግሎት ከሚመጣው ወይም የመምጣት እድል ካለው የህዝብ ቁጥር 3% ወይም 500 ግለሰቦች ያነሰው፣ ከሆነ የወሳኝ ኩነት መረጃዎች ኤል.ኢ.ፒ.ው ወይም ኤን.ኢ.ፒ.ው ማህበረሰብ በሚናገረው ቋንቋ የጽሁፍ ትርጉም እንዲሰጥ ያስገድዳሉ።

**ኤል.ኢ.ፒ. ና ኤን.ኢ.ፒ. ማህበረሰቦች በከተማዋ የሚሰጡ ወሳኝ አገልግሎቶችና ጥቅማ ጥቅሞች ዘንድ ተደራሽነት እንዲኖራቸው ለማረጋገጥ ዲ.ዲ.ኦ.ቲ. እንደነ የጽሑፍ ትርጉም (ትራንስሌሽን) እና የንግግር ትርጉም (ኢንተርፕሪቴሽን) የመሳሰሉ የቋንቋ እርዳታ አገልግሎቶች ያቀርባል።**



